**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**
**Ethiopian Peoples Revolutionary Party (EPRP)**

## የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ መግለጫ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ከኅዳር 15 እስከ ኅዳር 17 ቀን 1999 ዓም መደበኛ ስብሰባውን (plenum) በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል፡፡ ኮሚቴው ኢትዮጵያ ያለችበትን ልዩ የኤኮኖሚ፥ የፖለቲካና የማህበራዊ ሁኔታዎች መርምሮ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ በየእለቱ እያሽቆለቆለ መሄዱን፥ የገቢ ምንጮቹ እየደረቁና የሸቀጦች ዋጋ እየናሩ መሆናቸውን አጢኗል፡፡ ይህ በመለስ ዜናዊ የሚመራው አሸባሪና አምባገነናዊ መንግስት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈጽማቸው ግፎችና በደሎች ከእለት ወደ እለት እየመረሩና እየከፉ መሄዳቸውን፥ ግድያዎች መባባሳቸውንና በግፍ የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች ፍትህ መነፈጋቸውን ከምሬት ጋር ተገንዝቧል፡፡ ሕዝብን ከሕዝብ በማጋጨትና የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮችን በማፋጀት በማከተም ላይ ያለችውን የግፍ አገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም ብዙ ወንጀሎችን እየፈጸመ መሆኑንም መዝግቧል፡፡

በቅርብ ጊዜ ለህይወታቸው ብለው ከአገር ሸሽተው የወጡ፥ ከግንቦት 1997 ዓም ምርጫ በኋላ የተካሄደውን ጭፍጨፋ ለማጣራት በሕወሓት መንግስት የተቋቋመው የመርማሪ ኮሚሽን አባላት ያቀረቡትን የምርመራ ውጤት በኃይል ተጽኖና በተራ ማጭበርበር ለውጦ የዓለም ኅብረተሰብን ለማሳሳት ከንቱ ጥረት ማድረጉንና ለዚህም እርቃኑን መቅረቱን ታዝቧል፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝ መደበኛ ስብሰባው ኢትዮጵያን በቀጥታ የሚመለከቱ አካባቢያዊና ዓለምአቀፋዊ የፖለቲካ ሁኔታዎችንም በጥልቀት መርምሯል፡፡ በሱማሊያ ውስጥ እየተከሰተ ያለው አክራሪ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴና ተባባሪ መንግሥቶች በአንድ በኩል፥ የባእዳን ጥገኛ የሆነዉ የመለስ አገዛዝ የሚከተለው ወታደራዊና ፖለቲካዊ ጣልቃገብነት በሌላ በኩል ኢትዮጵያን ሊጎዱ የሚችሉ ከፍተኛ አካባቢያዊ ሁከቶች ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ አስገብቷል፡፡ እንዲሁም ባእዳን መንግሥቶች በፀረ አሸባሪነት ድጋፍ ሽፋን በአካባቢው የሚያካሄዱት ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችም ኢትዮጵያን ከአካባቢው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ አገሮችና መንግሥቶች ጋር የሚያጋጩና የሚጎዱ መሆናቸውን ተገንዝቧል፡፡

ይህ የኢሕአፓ አመራር መደበኛ ስብሰባ ከተለያዩ የድርጅቱ አካላትና አካባቢዎች የቀረቡትን ዝርዝር ዘጋባዎች አዳምጦና መርምሮ በርካታና ጠቃሚ የፖሊሲ ዉሳኔዎችን፥ የመዋቅር መስተካከሎችንና የትግል መርሆ መሻሻሎችን አድርጓል፡፡ አገራችንና ሕዝባችንን እየጠበቁ ያሉትን አደጋዎችን ለማክሸፍ፥ የሕግ የበላይነት ተከብሮ ሕዝቧ በሰላም፥ በፍቅርና በመከባበር የሚኖሩባትን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት የፓርቲው አራተኛ ጉባዔ የወሰናቸው የትግል ዘዴዎቹና መርሆዎች በተጠናከሩና በተሻሉ መንገዶች በተግባር የሚተረጎሙባቸውን የትግል ዘዴዎችና ዘላቂ ትልሞች ቀይሷል፡፡ እነኝህን የትግል አላማዎቹን ከግብ ለማድረስ፥ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሕዝብ ድል ለማረጋገጥ፥ የትግሉን ጊዜ ለማሳጠርና ሊደርሱ የሚችሉትን ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳቶችን ለመቀነስ ከኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር የትግል ተባሪነቱንና አጋርነቱን እንደገና አረጋግጧል፡፡

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን (ኢዴኃኅ) ስለማጠናከር በሰፊው ተወያይቶ የኅብረቱ ብሔራዊ ሸንጎ ሁለተኛ አስቸኳይ ጉባዔ በወሰነው መሠረት የፓርቲው አመራር ኮሚቴ የሚጠበቅበትን በሙሉ ለማድረግ ቃል ገብቷል።

ፓርቲው ያለማቸውን የትግል ግቦች እውን ለማድረግ ለውስጣዊ መጠናከርና መስፋፋት ት ኩረት ሰጥቷል። በዚህም መሠረት በአባላቱና በአካላቱ መካከል መኖር ሰለሚገባቸው የሥራ ግንኙነቶችና ተግባሮች አስፈላጊ መመሪያዎችን ሠጥቷል። በተለያዩ አካባቢዎች ላሉት የፓርቲ አካሎች የተቀላጠፈ የሥራ ቅንብር የሚያመቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችሉ እርምጃዎች በየደረጃው እንዲወሰዱ ውሳኔ አድርጓል።

ኢሕአፓ አሁንም እንደቀድሞው ሕዝቧን በሰላምና በእኩልነት ለማኖር የምትችለውን ኢት ዮጵያን ለመመሥረት ለኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶችና ለሲቪክ ማኅበረሰቦ ች የትግል ጥሪውን ያቀርባል። እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ለመብቱና ለነፃነቱ የሚያደርገውን ትግሉን እንዲያፋፍም ጥሪውን ያቀርባል። ኢሕአፓም እንደወትሮው ከሕዝቡ ጎን ይሰለፋል።

**አንድነቷን የጠበቀች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**

**ኅዳር 17 ቀን 199**

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
USA
Tel: (202)-291-4217
Fax: (202)-291-7645
E-mail: ESPIC@aol.com

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
FRANCE

Website: http://www.EPRP.com

EPRP
Postbus 1253
1000 BG Amsterdam
HOLLAND